QuickNotes mcps

## አዲሱ የትምህርት አመት በታላቅ አጀማመር ላይ ይገኛል

MCPS ሰኞ ኦገስት 26 ከዚህ ቀደም ታይቶ ለማይታወቅ የተማሪዎች ቁጥር በሮችን ሲከፍት፣ የ2013-2014 የትምህርት አመት በታላቅ አጀማመር ይገኛል። በዚህ አመት የዲስትሪክቱ 202 ትም/ቤቶች ከ151, 000 በላይ ተማሪዎች እንደሚያስተናግዱ ይጠበቃል፣ ይህም ከ2012-2013 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ቁጥር በ2,300 አካባቢ ከፍ ብሏል ማለት ነው። ባለፉት አምስት አመታት የተማሪዎች ምዝገባ ከ10,000 በላይ አድጓል እናም በ2018-2019 የተማርዎች ቁጥር 159,000 እንደሚያልፍ ይጠበቃል። MCPS አዲሱን አመት ከ38 አዲስ ርእሰ መምህራን እና ከ800 በላይ የሚሆኑ አዲስ አስተማሪዎች ጋር እየጀመረው ነው።

ዲስትሪክቱ እያተኮረ ያለው ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬታማነት የሚያስፈልጓቸውን እውቀትና ሞያዎች ለተማሪዎች ማስታጠቅ ላይ ነው እናም የዚህ አመት ትኩረት ስራውን ከአዲሱ ስልታዊ የፕላን መዋቅር—የወደፊታችንን አብረን እንገንባ ከሚለው መርህ ጋር ማስተካከል ነው።

ወላጆችና ተማሪዎች የሚወዷቸውን ፎቶግራፎች የትምህርት መጀመሪያ ቀን ሰኞ እንዲያስገቡ ተጋብዘው ነበር። MCPS ከ100 በላይ ተቀብሏል፣ እነዚህን የመጀመርያ ቀን ፎቶዎች መደርደርያ ለማየት እዚህ ይችላሉ።

ሰኞ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት፣ ከ7,000 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ለMCPS የትምህርት መጀመርያ አመታዊ በአል ኦገስት 24 ሮክቪል በሚገኘው የካርቨር የትምህርት አገልግሎት ማእከል ግቢውን ሞልተውት ነበር።

ወላጆች ከMCPS ሰራተኞች ለመገናኘት፣ ስለ ትም/ቤቱ ስርአት ፕሮግራሞችና ግብረቶች ለመማር፣ እና ስለ ማህበረሰቡ መገልገያዎች መረጃ ለመቅሰም እድል ነበራቸው። በዚህ በአል ጎልተው የሚታዩ የተማሪዎችና የማህበረሰቡ ቡድኖች ትርእይቶች፣ ነፃ የጤና ምርመራ፣ እና የልጆች ማዝናኛዎችና ግጥሚያዎችን ያካትታሉ።

MCPS Momentን በትምህርት መጀማርያ በአል ይመልከቱ

## አምስት ጥያቄዎች ... ለሜሪ ሃውኪንስ-ጆንስ፣ በአሜሪካ እጅጉን የላቀች ባለተስፋ መምህር

ሜሪ ሃውኪንስ-ጆንስ፣ በዌስትኦቨር ኤሌሜንታሪ ትም/ቤት የአምስተኛ ክፍል አስተማሪ በጋሉፕ ኢንክ. እና አትርያ መፃህፍት በአሜሪካ እጅጉን የላቀች ባለተስፋ መምህር ተብላ ተሰይማለች። የMCPS QuickNotes ስለ ማስተማር ያላት ተመስጦና ስለ ተስፋ ሃይል ከሜሪ ሃውኪንስ-ጆንስ ጋር ለማውራት እድል ነበረው።

### አስተማሪ ለመሆን ፍላጎት እንዳለሽ መቸ ተገለፀልሽ?

የ12 አመት አካባቢ ልጅ ሳለሁ። እናቴ የሰዎችን ቤቶች ታፀዳ ነበር። በሰመር ወራት ከሷ ጋር ለመስራት እሄድ ነበር። ከሴት ወይዘሮዎቹ አንዷ ሱዚ የምትባል የ2 ወይም የ3 አመት ልጅ ነበራት። እመቤትዋ ፊደል፣ ቁጥሮችና ቀለሞችን ላስተምራት እችል እንደሆን ጠየቀየችኝ። ስራዬ ከሱዚ ጋር መጫወትና መሰረታዊ ነገሮችን ማስተማር ነበር። ከአንድ ሁለት አመት በኋላ

እናቴ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሰንበት ትምህርት ለልጆች ማስተማር እፈልግ እንደሆን ጠየቀችኝ፡፡ ስለሱዚም አስታውሳ ጥሩ ስራ እንደሰራሁ ነገረችኝ፡፡ ያ ነው አንጎሌ ውስጥ እንደገደል ማሚቶ የተንፀባረቀው፡፡

እኔ ቤተሰብ ውስጥ፣ ለማድረግ የፈለግነውን ሁሉ፣ ወላጆቼ ያበረታታሉ፡፡ ፕላን እንድናወጣና እሱን ተግባራዊ እንድናደርግ በቀጥታ ይነግሩን ነበር፡፡ ገደቦች አሉ ብለው ምንግዜም ነግረውን አያውቁም፡፡

**በስራሽ ከሁሉም ይበልጥ የሚያረካሽ ምንድን ነው?**

ከሁሉም የሚበልጠው ሽልማት የወደፊቱን ማየት ነው፡፡ ተማሪዎቹን የማስተምቸራው ባሁኑ ወቅት እንኳን ለሌሉ የስራ አይነቶች ነው፡፡ ተስፋ ልሰጣቸው ከቻልኩና ግንኙነቶችን እንዴት እንደሚያደርጉ ላስተምራቸው ከቻልኩ፣ መማር የሚያዛቸውና ለነሱም የሚጨበጥ ሃቅ ከሆናቸው፣ ስለወደፊት ምንም ያሚያሳስበኝ አይኖርም፡፡ ታላቅ ይሆናል፡፡ በአመቱ መጨረሻ፣ የወደፊቴን ማየት እችላለሁ ፈገግታም ይሰማኛል፡፡

**ተስፋ ለምንድነው ያን ያክል መሳጭ የሚሆነው፣ በትምህርትስ ምን ሚና አለው?**

ያለኝን ሁሉ ስሰጥ ያን ግዜ አውቀዋለሁ፣ ለወደፊት መልሰው ይሰጡኛል፡፡ በማስተምርበት የመጀምርያ አመቴ፣ ክሪስቲና ኡልሪከን (በ2012 የMCPS የአመቱ አስተማሪ) በላንግሌይ ፓርክ ማክርሚክ ኤሌሜንትሪ ትም/ቤት (ፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ) አስተምሪያታለሁ፡፡ ክሪስቲና በጣም ጎበዝ መምህር ናት፡፡ በሷ ወደፊት ትንሽ ሚና እንደተጫወትኩ ማወቄን እወደዋለሁ፡፡ አሁን ደግሞ፣ እሷ ለተማሪዎቿ ያንኑ እያደረገች ነው እናም ምንም እንኳን ተማሪዎቿን ባላውቃቸውም፣ በህይወታቸው ድርሻየን እየተጫወትኩ ነው፡፡ ስለዚህ ቀጣይ የሆነ ተፅእኖ በወደፊት አለኝ፡፡ ይህ ያ ትንሹ የተስፋ ሞገድ ነው፡፡

**ወላጆች በልጆቻቸው ተስፋ ለማስረፅ ምን ማድረግ ይችላሉ?**

ሞዴል/አረአያ መሆንና ልምምድ የተስፋ ማስረፅያ ቁልፎች ናቸው፡፡ ልጆቻቸውን ለማጎልበትና ለማንኛውም ችግር ከአንድ በላይ መፍትሄ እንዳለው እንዲያምኑ ወላጆች ተስፋን ለልጆቻቸው ሞዴል ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ልጆችዎን ስለወደፊት ያነጋግሯቸው፡፡ ስለ ግቦቻቸውና ስለ ህልሞቻቻአው ጠይቋቸው፣ እነሱንም ተግባራዊ ለማድረግ ከነሱ ጋር አብረው ይስሩ፡፡ ወላጆቼ ትምህርትን ከፍተኛ ዋጋ ይሰጡት ነበር፡፡ ትምህርት ለተስፋዎቼና ለህልሞቼ ቁልፍ መሆናቸውን አስተማሩኝ፡፡

**ለተማሪዎችሽ ተስፋሽ ምንድን ነው?**

ሁሉም ተማሪዎች በራስ መተማመንና በራስ ተነሳሽነት ሁሉንም ጥረቶች እንዲጋፈጡ የኔ ተስፋ ነው፡፡

MCPS Momentን በሜሪ ሃኪንስ-ጆንስ ይመልከቱ

**የትም/ቤቶቻችንን ደህንነት መጠበቅ ላይ ያግዙን**

ደህናና ጤናማ የትም/ቤት አካባቢ ላይ ማንም ሰው አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡ አብዛኛውን ግዜ፣ የወላጆችና የተማሪዎች ጥቆማዎች የወጣቶች ሁከት፣ የእፅና ያልኮል ብልሹና፣ የወንበዴ ተሳትፎ እና ከሌሎች የተማሪዎች ደህንነት አደጋዎች ለመከላከል ያስችላሉ፡፡ MCPS ዛቻዎች፣ ወይም የደህንነትና የፀጥታ ሁከቶች ማመልከቻ ምስጢራዊ Safe Schools Hotline (አስተማማኝ ትም/ቤቶች ልዩ መስመር) መገናኛ አሉት፡፡ 301-517-5995 በቀን 24 ሰአት/በሳምንት ሰባት ቀኖች መደወል ይችላሉ፡፡ አንድ አጠራጣሪ ነገር አይተው እና/ወይም ሰምተው ለማሳወቅ የሚፈልጉ ተማሪዎች በ274637 (CRIMES) የጥቆማ ቴክስት Text-a-Tip ማድረግ ይችላሉ፡፡

ወላጆች ስለMCPS የደህንነት ቅደም ተከተሎች በ[Safety and Security ድረገፅ ](#)በመጎብኘት እንዲማሩ እናሳስባለን። በቦታው የሚገኙ ቪድዮዎች በlockdown (ዝጋ)፣ shelter in place (መጠለያ ቦታ) እና evacuation (ለቀህ ውጣ) የሚያካትቱ ስለ ትም/ቤት ፀጥታ ሂደቶችና ፕሮቶኮሎች ያብራራሉ። ስለ ኮምፒውተር ደህንነት፣ ላስቸኳይ ሁኔታ ዝግጁነት እና ሌላም ሌላም ተጨማሪ መረጃዎች አሉ።

በትም/ቤት ንብረት ውስጥ፣ በትም/ቤት አውቶብስ፣ ወይም ትም/ቤት ስፖንሶር በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚደርሱ የቡሊዪንግ (አቅመቢስ ላይ መደንፋት)፣ ማስጨነቅ እና የማስፈራራት ተግባሮች ተማሪዎችና ወላጆች እንዲያሳውቁት MCPS ያበረታታል። ቡሊንግ የቃል፣ አካላዊ፣ ወይም የፅሁፍ (ኤሌክትሮኒክን ጨምሮ) እናም በተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በቅርብ አዋቂ ዘመዶች እና በትም/ቤት መምህራን/ሰራተኛ አባላት ሊመለከት ይችላል። ለርእሰ መምህሩ/ሯ ገቢ የሚደረጉት ዘገባዎች በ[Bullying, Harassment or Intimidation Reporting Form ](#)በኩል ሊመለከቱ ይቻላል።

## የተማሪ አመራርና አገልግሎት እድሎች

የMCPS የስርአተ ትምህርት አማካሪ ቡድን እና የሜሪላንድ የተማሪ ገፅ ፕሮግራም (Maryland Student Page Program) ማመልከቻዎችን አሁን እየተቀበሉ ነው። ለተሟላ የእድሎች ዝርዝር፣ ተማሪዎች [Student Affairs ድረገፅ](#) እንዲጎበኙ ይበረታታሉ።

### የMCPS ስርአተ ትምህርት አማካሪ ቡድን

በየአመቱ፣ የተማሪ ጉዳዮች መምርያ በAssociate Superintendent’s Curriculum Advisory Assembly (የበላይ ተቆጣጣሪ ተባባሪ የስርአተ ትምህርት አማካሪ ቡድን) የተማሪ ክፍት ቦታዎች ለመሙላት ፈቃደኛ የሆኑ እጅጉን የላቁ ተማሪዎች ስሞች ይሰበስባል። በዚህ አመት፣ በ 7ኛና በ10ኛ ክፍሎች ለሚገኝ ተማሪ አንድ ክፍት ቦታ አለ።

የስርአተ ትምህርት አማካሪ ቡድን ግቦች የሚከተሉት ናቸው:-

- ስርአት ትምህርትን፣ ትምህርት አሰጣጥን፣ ግምገማዎችን፣ እና ፕሮግራሞችን በሚመለከት ከአባላት አስተዋፅኦና አስተያየት ማግኘት።

- ስርአተ ትምህርትን፣ ትምህርት አስጣጥንና ግምገማን ስለሚመለከት ከስቴትና ፌደራል ደንቦች፣ እና ስርአት አቀፍ ተቀዳሚ ጉዳዮች አባሎችን ወቅታዊ መረጃ መስጠት።

ከተመረጡ፣ ተማሪዎች ምንግዜም ማስታወስ ያለባቸው፣ ቦታውን መቀበል ማለት ሁሉንም ስብሰባዎች የመከታተል ግዴታ ማካተቱን ነው። ተማሪዎች ለሁሉም ስብሰባዎች መድረሻና መመለሻ የራሳቸውን ማጓጓዣ ማቅረብ አለባቸው።

በአማካሪ ቡድኑ ለቀረቡት አገልግሎት ተማሪዎች Student Service Learning (የተማሪ አገልሎት ትምህርት) ሰአታት ያተርፋሉ። ለተጨማሪ መረጃና ለማመልከት፣ [እዚህ ጠቅ ያድርጉ](#)

### የሜሪላንድ Student Page (የስቴት እንግዳ ተቀባይ) ፕሮግራም ማመልከቻዎች አቀባበል

የሜሪላንድ Student Page (የስቴት እንግዳ ተቀባይ) የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት የመጨረሻ ክፍል ተማሪዎች ለ2014 የሜሪላንድ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይፈልጋል። ቢያንስ 16 አመት የሞላቸው የሜሪላንድ የከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች ለማመልከት ብቁ ናቸው። እንግዳ ተቀባዮች በስኔት ወይም በሃውስ ኦፍ ደለጌትስ ለ13 ሳምንቶች ይመደባሉ ለያንዳንዱ ያገለገሉበት ቀን $55

የኪስ ገንዘብ ይሰጣቸዋል። የማመልከቻ የግዜ ገደብ፣ አርብ ኦክቶፐበር 25 4 p.m. ነው። ማመልከቻ ቅፆችMCPS Office of Student Affairs ድረገፅ ይገኛሉ።

የተሞሉ ማመልከቻዎች ወደ Karen Crawford, 12900 Middlebrook Road, Germantown, MD 20874 መላክ አለባቸው። ተጨመሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።

## Consortia News

The Northeast (NEC) and Downcounty (DCC) consortia (የተወሰኑ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ጥቅል ስም) የ2ኛ ደረጃ ማመልከቻ ፕሮግራሞች በሴፕቴምበርና በኦክቶበር የመረጃ ስብሰባዎች ያካሂዳል። NEC ወይም DCC የሚኖሩ ተማሪዎች ስለ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች አማራጮች፣ ኮንሶርሲያ ትም/ቤቶች፡ የChoice ሂደትና ልዩ የማመልከቻ ፕሮግራሞች መረጃ ያገኛሉ። ማመልከቻዎች በሰፕቴምበር መጨርሻ ላይ በትም/ቤቶችና በMCPS ድረገፅ ይገኛሉ።

በኤሌሜንታሪ የከፍተኛ ተሰጥኦ ማእከሎች ለመማር የሚፈልጉ የ3ኛ ክፍል ተማሪ ቤተሰቦች በኦክቶበር ወር የመረጃ ስብሰባዎች ተዘጋጅተዋል። ማመልከቻዎች ወደየቤታችሁ በሰፕቴምበር ወር በፖስታ ይላካሉ በድረ ገፁም እንዲገኙ ይደረጋል። በመካከለኛ ትም/ቤት ማግኔት ኮንሶርቲየምና የመካከለኛ ትም/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራሞች ለመማር ፍላጎት ላላቸው የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችና ወላጆቻቸው የሚ ሆኑ የመግለጫ ስብሰባዎች በሴፕቴምበርና በኦክቶበር በፕሮግራም ተይዘዋል። ማመልከቻዎች በሴፕቴምበር መጨርሻ ላይ በትም/ቤቶችና በMCPS ድረገፅይገኛሉ።

## በኮምቲውተር ያለንን የፈተና መዘጋጃ (Online Test Prep) ተጠቀሙበት

ለሚመጡት PSAT፣ SAT ወይም ACT ለመዘጋጀት ተማሪዎች ኮምፒውተር ላይ በነፃ በሚገኙት መሳርያዎች መጠቀም ይችላሉ። ስለፈተናዎቹ በተጨማሪ ለማወቅ፣ የተወሰኑ ሞያዎችን ድህረ እይታ ለማድረግ፣ የመለማመጃ ጥያቄዎች ለሚወስዱና ግስጋሴአቸውን ለመከታተል የሚፈልጉ ተማሪዎች እነዚህን መሳሪያዎች በማንኛውም ጊዜ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

የPSAT ፈተና ዝግጅት

የSAT ፈተና ዝግጅት

የACT ፈተና ዝግጅት

የፎል ወራት የፈተና ቀኖች የሚከተሉት ናቸው:-

SAT

- ኦክተበር 5
- ኖቨምበር 2
- ዲሰምበር 7

ACT

- ሴፕተምበር 21
- ኦክተበር 26
- ዲሰምበር 14

PSAT

- ኦክተበር 16
- ኦክተበር 19

**የቤተመፅሃፍ ካርድ ማውጫ ማንኛውም ግዜ ትክክለኛው ግዜ ነው።**

ሴፕተምበር የቤተመፅሃፍ ካርድ ተመዝግቦ የሚወሰድበት ወር ነው፣ የህንንም በመዘከር Montgomery County የህዝባዊ ቤተመፅሃፍቶች (MCPL) በማንኛውም የእድሜ ደረጃ የሚገኙ ነዋሪዎችን የቤተመፃህፍት ካርድ ከሁሉም የላቀች ካርድ ቦርሳ ውስጥ፣ የጀርባ ቦርሳዎ፣ የቁልፍ ማያዣዎ ወዘተ ካሉት በላይ መሆኗን ያስታውሳል - ለዛውም በነፃ!

የቤተመፃህፍት ካርድ ለብዙ ተሞክሮዎች ቁልፍ ናት—የምትወዷቸውን መፃህፍት ለማንበብ፣ ለመቁጠር በሚያዳግቱ ብዙ ርእሶች ምርምር ለማካሄድ፣ ሙዚቃ ለመስማት፣ አዲስ ቋንቋ ለመማር፣ እና አዳዲስ ሙያዎች ለመልመድ ታገለግላለች።

ዝርዝሮችን በwww.montgomerycountymd.gov/library ይመልከቱ እና ወደ አካባቢዎ ቅርንጫፍ ሄደው ይመዝገቡ። ላዲስ ካርድ ሴፕቴምበር ሲመዘገቡ ልዩ "እናመሰግናለን" ይቀበላሉ።

**Race for Every Child (እሽቅድድም ለያንዳንዱ ልጅ)**

The Race for Every Child (እሽቅድድም ለያንዳንዱ ልጅ) በዋሺንግተን አካባቢ ልጆችንና ቤተሰቦችን ለመደገፍ ተብሎ የሚከናወን መዝናኛ ነው። ድርጊቱ ለልዩ የህክምና እንክብካቤ፣ ለህፃናት በሽታዎች ምርምር፣ እና Children’s National Medical Center (የልጆች ብሄራዊ የጤና ማእከል) አማካኝነት ሁሉንም ልጆች ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ የጤንነትና የመከላከያ አገልግሎቶች የገቢ ምንጭ ነው።

ሩጫው፣ መራመድና Kids’ Dash ቅዳሜ ኦክቶበር 5 2013 በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ፍሪደም ፐላዛ (Freedom Plaza in Washington, D.C.) ይከናወናል። ድርጊቱ የሚጀምረው በ7 a.m. የሚያልቀውም በ1 p.m. ነው።

ተሳታፊዎች፣ ስፖንሰሮች፣ እና ተባባሪዎች የታወቁ የህፃናት ሃኪሞችን ለመገናኘትና በብሄራዊ የልጆች ጤና ማእከል ህክምና ያገኙ ልጆች እንዴት በመፋፋት ላይ ስለመሆናቸው ቀስቃሽ የሆኑ ታሪኮች ለመስማት እድል ይኖራቸዋል።።

ለተጨማሪ መረጃ Race for Every Child ድረገፅ ይጎብኙ።

**Montgomery County መዝናኛ የሚገኙ የፎል ወራት ፕሮግራሞች**

የMontgomery County Guide for Recreation and Parks Programs (የመዝናኛና የመናፈሻ መመርያ) የፎል ህትመት አሁን ማግኘት ይቻላል። ብዙ ፕሮግራሞች ቶሎ ስለሚሞሉ የMontgomery County ነዋሪዎች ቶሎ እንዲመዘገቡ እናደፋፍራለን። መመርያው በሎቶዎች የሚቆጠሩ ለቤተሰብ በሙሉ የሚሆኑ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ይዘረዝራል። የውሃ ስፖርት፣ የፈጠራና የሚታዩ ኪነ ጥበባት፣ እና ስፖርቶች ከወጣቶች አማራጮች ጥቂቶቹ ናቸው።

መመርያውን በኮምፒውተር ለማየት Department of Recreation ድረገፅ ይጎብኙ።  የታተሙ ቅጂዎች በመዝናኛ ማእከሎች፣ በመናፈሻ መገልገያዎች፣ በመንግስታዊ ህንፃዎችና ቤተመፃህፍት ይገኛሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ 240-777-6840 ይደውሉ።

ጌተርስበርግና የሮክቪል ከተሞች ለልጆችና ለአዋቂዎች ብዙ መዝናኛዎች አሏቸው። ለተጨማሪ መረጃ ፡-

- Gaithersburg መናፈሻዎች፣ መዝናኛ፣ እና ባህል
- Rockville መዝናኛዎችና መናፈሻዎች